ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት. ዴ. ፓ)
Tigray Democratic Party (T.D.P)

# ሕገ-መንግስትን የማያከብር ምርጫ፣ ለምን ?

በስራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት አፍላቂ፣ አርቃቂ፣ ፀሓፊና አጽዳቂ የህወሓት መሪዎች ለመሆናቸው ማንም ሰው አይስተውም። ሆኖም የህወሓት መሪዎች እራሳቸው የፈጠሩት ሕገ-መንግስት መሆኑን የረሱት እስኪመስል ድረስ አጣመው ሲተረጉሙትና ሲሸሹት አልያም ሲጥሱት ማየቱ የተለመደ ሆኖዋል። ገና ስልጣን ላይ እንደወጡ በ1983 ዓ/ም ጀምሮ የባሕር በር ጥያቄ ያቀረቡትን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በመግደል ነበር የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰቱን የጀመሩት። ከዚያኑ ጀምሮ አፈናው፣ ድብደባው፣ ግድያውና ያለፍርድ እስራቱ አሁን ድረስ ቀጥለውበታል። ይህ እንደ መደበኛ አሰራር ያዳበሩት ክፉ ልምድ ብሎ-ብሎ አሁን አደገኛ ጫፍ ላይ በመድረሱ ሰላም፣ አንድነት፣ እኩልነትና ዕድገት የጠማው የኢትዮጵያ ህዝብ ተግቶ መፍትሄ ይሻ ዘንድ ይህን መግለጫ ማውጣት ግድ ሆኖብናል።

በቅድሚያ የወቅቱ አሳሳቢ ጉዳይ በሆነው ከሃገራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ ሕገ-መንግስቱ የደነገገውና የህወሓት መሪዎች የሚሉትን በንፅፅር እንመልከት። በአንቀጽ 102 መሰረት፣ ሕገ-መንግስቱ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን ማቋቋሙንና ቦርዱም **በፌደራልና በክልል** ደረጃዎች ምርጫን የማስፈጸም ሃላፊነት እንደተሰጠው በግልጽ አስቀምጧል:: ሕገ-መንግስቱ እንዲህ ቢልም በአንጻሩ የህወሓት መሪዎች ግን የክልሉ ምርጫ በገዛ እጃችን እናካሂዳለን ብለው ደፋ-ቀና እያሉ ይገኛሉ። ለምን? መልሱ ቀላልና የማያሻማ ነው። ባጭሩ እነሱ ያቀናበሩት ምርጫ ከተካሄደ እነሱ እራሳቸው አሸናፊዎች ተብለው ስልጣን ላይ እንደገና ብቅ እንደሚሉ ካለፉት ምርጫ ተብየ ቅንብሮችና "ተውኔቶች" ስለሚያውቁት ነው።

በዚህ ጊዜ በትግራይ ይቅርና፣ በመላ ኢትዮጵያ ምርጫ በምንም መልኩ ማካሄድ የሚችልበት ማኅበራዊ ብሎም ሕገ-መንግስታዊ ምክንያት እንደሌለው በመግለፅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማያሻማ መንገድ ገልጾላቸዋል። በጥቂት አምባገነን መሪዎች የሚዘወረው የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ግን ከዚህ ውሳኔ በፊትም ጀምሮ የትግራይ ፖለቲካዊ ምሕዳር ጥፍንግ አድርጎ በመያዝ የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳውን የባሰ ዘግቶት የክልሉ ምርጫ ያለ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አካሂዳለሁ እያለ ይገኛል። ራሱን የመሰሉ ምስሌነ ድርጅቶች በመፈልፈል መጫወቻ ሜዳው ዴሞክራሲያዊ፣ ምርጫውም ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የተሳተፉበት ለማስመሰል ላይ ታች እያለ ነው። እነዛን ራሱ የፈለፈላቸው ምስሌነ ድርጅቶች ከፋይናንሳዊ እገዛ ጀምሮ ፅ/ቤቶች እንዲከፍቱ፣ በክልሉ ቴሌቪዥኖች እና ኤፍ ኤም ሬድዮዎች እንደፈለጉት እንዲለፍፉ እና ተፎካካሪ መስለው በመቅረብ ህዝብን እንዲያደናግሩ ሁኔታዎች አመቻችቶላቸዋል።

በሌላ ወገን ደግሞ ሌሎች ሕጋዊና ራሳቸውን የቻሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ትግራይ ውስጥ ገብተው የፖለቲካ ስራዎች እንዳያሳልጡ በአምባገነኑ የህወሓት መዋቅር ብዙ እንቅፋቶች ተፈጥሮባቸዋል። ከፍረጃ ጀምሮ፣ ለጀሮ የሚከብዱ ስሞችን/ስድቦችን በመለጠፍ፣ ስብእናን በመግደል፣ አባላቶቻቸውን በመደብደብና በማሰር፣ ፅ/ቤቶች እንዳይከራዩ ከተከራዩም በማዘጋት የትግራይ ፖለቲካ ምህዳር በባሰ መልኩ ዘግቶታል። የህዝብ ንብረት በሆኑት የትግራይ ሚድያዎች መቅረብ እማ ለነዚህ ፓርቲዎች የማይታለም ነው። እንዲያው ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ በሕገ-መንግስቱ ከፍል አንድና ሁለት፣ ከአንቀጽ 14 እስከ 32 ያሉትን የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ድንጋጌዎች በመሉ ተጥሰዋል ማለቱ በቂ ነው።

በዚህ ግዜ ደግሞ የፖለቲካ ምህዳሩን የባሰ በመወጠር የህወሓት አምባገነን መሪዎች:-

1. የ2012 ዓ/ም ክልላዊ ምርጫ ከማድረግ የሚያግደን ምንም ኃይል የለም በሚል ስርዓት-አልባ ውሳኔ አሳልፈው ከፍተኛ የሚድያ እና የአድርባይ ካድሬ ዘመቻዎች ጀምሯል። በሃገራችን ማናቸውም ከፍል ምርጫን የማካሄድና የመምራት ሕገ-መንግስታዊ ሉአላዊ ስልጣን የተሰጠውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን አልቀበልም ብለው ክልላዊ ምርጫውን ለማካሄድ እየዛቱ ይገኛሉ።
2. እነዛ የምርጫ ቦርድ ምስክር ወረቀት እንኳን የሌላቸውን እና የፈለፈሉዋቸውን ምስሌነ ፓርቲዎች በማሳተፍ እንዳለፉት 5 ምርጫዎች የውሸት ምርጫ በማካሄድ አሁንም የትግራይ አይነኬ ገዢዎች ለመሆን በመቋመጥ ወገባቸውን አስረው እየሰሩ ነው።

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-940-79-08-22/+251-914-73-35-39
Website: tigraydemocraticparty.com, email: tigraydemocraticparty@gmail.com
ልደታ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 53፣ ፓፓሲኖስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 909/33፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 59፣ መቐለ

3. አሃዳዊና ጨፍላቂ መንግሥት መጣብህ በማለት በባሰ መልኩ ህዝቡን በማደናገርና በማስፈራራት ህዝቡን ከፌደራል መንግስቱ ጋር ጦርነት ውስጥ ለማስገባትና በሰበቡ ሥልጣንቸውን ለማራዘም በሚል ስሌት ቀቢፀ-ተስፋ እርምጃዎች በመሰንዘር ላይ ታች እያሉ ይገኛሉ።
4. በሌለ ጠላት «ተከበሃል» የሚል ልበ-ወለዳዊ ትርክት በመፍጠር ከጎረቤት ወንድም ህዝቦች ጋር ወደ ጦርነት ሊያስገቡት የጦርነት ነጋሪት እያወጁ ይገኛሉ።
5. በዚህ ሳምንት ደግሞ በትግራይ ያሉ የእውነተኛ ተፎካካሪ ፓርቲዎች አባላት ስም ዝርዝርን በማውጣት ህዝቡ በነዚሁ አባላት ላይ በሆነ መልኩ የማስወገድ እርምጃ እንዲወስድባቸው በማነሳሳት ላይ ይገኛሉ።
6. በሌላ በኩልም በመሐል አገር ያሉ አንዳንድ ፓርቲዎች በማፈላለግ ከአምባገነኑ የህወሓት አመራር ጋር እንዲወግኑ በማግባባት፣ በሁለቱ ምክርቤቶች የፀደቀውን የሕገ-መንግሥት ትርጉም ውሳኔን በህገ-ወጥነት እንዲቃወሙና አገሪቱን በማበጣበጥ በአቋራጭ ሥልጣንን ለመቆጣጠር ያለመ ህዝቡን የማደናገር እና ህዝቡ በፌደራል መንግሥቱ ላይ አሉታዊ ግንዛቤ እንዲኖረው እያደረጉ ይገኛሉ።

በትግራይ ክልል ያለው ወቅታዊ የፖለቲካ መስተጋብር ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሲሆን በአምባገነኑ እና «የበሰበሰው» የህወሓት አመራር የሚዘወረው የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት እስካሁን የሄደበት የፖለቲካ ጉዞ እጅግ ትእግስት የበዛበትና የሚመሰገን ነው። ሆኖም ግን ሙሰኛው እና ጨፍላቂው የህወሓት አመራር በተለይ ላለፉት ሁለት ዓመታት እየተጓዘበት ያለው መንገድ የትግራይ ህዝብንና ክልሉን ብቻ ሳይሆን የተቀረውን የኢትዮጵያ ሉአላዊነትንና ህዝቡን የሚጎዳ ብሎም የአገሪቱ ሁለንተናዊ ሰላም በመሸርሸር ላይ መሆኑ «ፌዴራላዊ ጥምረት» እያለ ከሚያስማራቸው ፀረ-ለውጥ ቡድኖች እንቅስቃሴ መገንዘብ አይከብድም። ይህ ሃገርን የሚያናጋ አደገኛ ሂደት በወቅቱ ካልተገታ ለእርስበርስ እልቂት የሚዳርግ ለመሆኑ እሩቅ ሳንሄድ ከጎረቤቶቻችን አናጣውም፤ በመሆኑም ***የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 51 ቁ 1 እና ቁ 6*** መሰረት ግዴታ ስላለበት፣ ለሃገር ደህንነት ሲባል ጊዜ ሳያባክን በዚህ መርዘኛ ቡድን ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት አበክረን እናሳስባለን።

## የትግራይ ህዝብ ሆይ፡-

በስምህና በልጆችህ መስዋእትነት እየማሉና እያላገጡ፣ በመላ ኢትዮጵያ አፈና፣ ሙስና፣ ድህነትና የርስበርስ ግጭት እንዲስፋፋ ያደረጉት ስግብግቦቹ የህወሓት መሪዎች የለውጥ አየር ስለመጣባቸው ወደ መቐለ በመሸሸ፣ «ጠላት መጣብህ! ተከበሃል! ታጠቅ! ተከላከል!» እያሉ እረፍት እንደነሱህ ራስህ ታውቀዋለህ። የከበበህም ይሁን የመጣብህ ጠላት የለም። ውሸት ነው። ይህ ሁሉ ውሸት ግን ዓላማ አለው። በመላ ኢትዮጵያ የነፈሰው የለውጥ አየር ትግራይ ውስጥ ተጋብቶ ህዝብ በነጻ ውይይት እንዳይለበልባቸው ለመከላከልና በለመዱት ስልጣን ላይ ለመሰንበት ታስቦ ነው። እነሱና ልጆቻቸው ስልጣንን መከታ አድርገው ባካበቱት ሃብት በምቾት ሊኖሩ፣ አንተና ልጆችህ ግን እየሞትክና እየቆሰልክ ተከላካይ ልትሆንላቸው አስልተው ነው። ለዚህ ነው «ህወሓትና የትግራይ ህዝብ አንድ ነው» እያሉ ጧትና ማታ የሚዘፍኑልህ።

ከዚሁ ጋር ተያይዞም፣ ተገንጥለን የራሳችን መንግስት (de facto state) መስርተን እንምራህ ይላሉ:: የ29 ዓመታት አስከፊ አገዛዛቸው መላው ኢትዮጵያዊ እንዳላንገሸገሸው ሁሉ፣ ኣሁንም ለብቻቸው ተነጥለው የክልል ምርጫ ለማካሄድና በለመዱት አፋኝ አገዛዝ ሊቀጥሉ ይንደፋደፋሉ። አንደኛ ነገር፣ ማን ከማን ነው የሚገነጠለው? የኢትዮጵያ ህዝብ በትውልድ፣ በታሪክ፣ በባህል፣ በስነ-ልቦና እንዲሁም በፖለቲካ-ኢኮኖሚ የተቆራኘና ለመገንጠል የማይቻል ህዝብ ነው። ከየት ወዴትስ ነው የሚገነጠለው? በስልጣን ያኮረፉ ሁሉ ልገንጠል ቢል ገደቡስ የት ላይ ነው? ሁለተኛ፣ የመገንጠል ፋይዳውስ ምንድን ነው? ሰላም፣ ፍትሕና ዕድገት ከተፈለገም ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመገንባት እንጂ በመገንጠል እንደማይገኙ እሩቅ ሳንሄድ ጎረቤቶቻችንን ማየት በቂ ነው።

ስለዚህ የተናጠል ምርጫ ማካሄድ ሕገ-መንግሥቱን የሚጥስ ከመሆኑ ባሻገር፣ ተነጥሎ ለመኖር ሽሽት ላይ ላሉት፣ ወኔ የራቃቸው ሙሰኞቹ የህወሓት መሪዎች ጊዜያዊ መደበቂያ ይሆናቸው እንደሆን እንጂ ለትግራይ ህዝብ ምንም ዓይነት እርባና እንደሌለው ሊታወቅ ይገባል። ትልቅ ሃገር እየገዙ ያላመጡት ሰላም፣ ፍትሕና ዕድገት፤ ትንሽ ሃገር መስርተው ያመጡታል ማለት ዘበት ነው። “ሌብነት ስራ ነው፣ ከተያዝክ ግና ወንጀል ነው” ብለው የሚስብኩ፣ “ለህክምና የተሰራ ህንፃ እዚህ ነበረ፣

አሁን ግን ጠፉ” ብለው ሪፖርት የሚያቀርቡ፤ እንደነ አለማት አማረ (የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ም/ሓላፊ) ለህዝብ መብት መከበር የቆሙትን ሁሉ “ባንዳዎች” ብላ የምትዘነጥል፣ ዋልጌ እና ምግባረ ብልሹ መሪዎች ፤ ሁሌም በመከራ፣ ስደት፣ ግጭትና አፈና ሊያኖሩህ ካልሆነ በስተቀር ለችግርህ መፍትሄ ስለማይሆኑ፣ እነሱን በሰላማዊ መንገድ በማስወገድ የራስህን ዕድል በራስህ ወሳኝ የምትሆንበትን ስርዓት ለመፍጠር ተደራጅተህ ታገል እንላለን። ሕጋዊነትና ዴሞክራሲያዊነት የሌለው ምርጫ ለሙሰኞችና ለአፋኞቹ መሪዎች ይበጅ እንደሆነ እንጂ ለህዝቡ የትም ስለማያደርስ ከወዲህ በግልጽ መቃወምና ያሰቡት የመንደር ምርጫው ማስቆም ያስፈልጋል። የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) ምን ጊዜም ከጎንህ ላይ ቆሞ፣ ሁሉንም በእኩልነት አሳታፊ ሕገ-መንግስታዊ ምርጫ ተካሂዶ፤ ሰላም፣ ፍትሕና ዕድገት፤ የሚሰፍንበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በኢትዮጵያ እንዲመሰረት ትግሉ በአጽንኦት ይቀጥላል።

**ድል ለህዝባችን !!**

**ውድቀት ለአምባገነን መሪዎች !!**

**ኢትዮጵያ ትለምልም !!**

**ት.ዴ.ፓ. .. .. .. ሰኔ 2012 ዓ/ም**


**ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-940-79-08-22/+251-914-73-35-39**
**Website: tigraydemocraticparty.com, email: tigraydemocraticparty@gmail.com**
**ልደታ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 53፣ ፖፓሲኖስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 909/33፣ አዲስ አበባ፣**
**ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 59፣ መቐለ**